# ልጅዎ ቅድመ-መዋዕለ-ልጻናት ገብቷል/ገብታለች

## ስለ አራት ዓመት ልጆች

4

በመማሪያ ክፍልም ይሁን በቤት ውስጥ በጣም ባተሌዎቹና ቅብጥብጦቹ ሕጻናት የአራት ዓመቶቹ ናቸው:: የዕድሜ እኩዮቻቸው ከሆኑ በርካታ ሕጻናት አካባቢ መሆንን ይፈልጋሉ፣ እናም ሁልጊዜ ለመሮጥ፣ ለመዝለል፣ ለመንጠላጠል፣ እና ለመግፋት ያላቸውን ሙሉ አቅም የሚጠቀሙ ይመስላሉ::

አንዳንድ ጊዜ የአራት ዓመት ልጆችን ለማወቅና ለመረዳት አስቸጋሪዎች ናቸው:: በአንድ የተወሰነ ደቂቃ ውስጥ በራሳቸው የሚተማመኑና ደፋር ይሆናሉ፣ እንደገና በሚቀጥለው ደቂቃ ላይ ድጋፍና ማጽናናት ይፈልጋሉ:: ለጋ ሕጻናት የሆነ ነገርን በመሞከራቸው መወደስን/መሞገስን፣ የራሳቸውን ዓለም እንዲዳስሱም መበረታታትን ይፈልጋሉ:: ይሁንና ለደህንነታቸው ተብለው የተበጁ ህግና ደንቦችን መከተል ይኖርባቸዋል:: የነጻነትና እራስን የመቻል ስሜትን በማዳበር አንዳንድ ምክንያታዊ የሆኑ ምርጫዎችን በራሳቸው እንዲመርጡ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል፣ ነገር ግን ጠንካራ ገደብም ሊደረግባቸው ይገባል::

በባህሪያቸውና በድርጊቶቻቸው ምክንያት የተጣለባቸውን ገድብ (አታድርግ የተባሉትን ለማድረግ) መፈታተን ለአራት ዓመት ሕጻናት የተለመደ ባህሪያቸው ነው:: በጥሩውና በመጥፎው መካከል ያለውን ልዩነት መማር ያስፈልቸዋል:: የትምህርት ቤት ደንብን እንዲከተሉና እንዲያከብሩ መበረታታት ያስፈልጋቸዋል፣ በሌላ በኩል ግን በነሱ በኩል የሚቀርበውን ታሪክም የሚያዳምጣቸው ሰው እንዲኖር ያስፈልጋቸዋል:: ያስታውሱ የአራት-ዓመት-ልጅ በአብዛሃኛው ተባባሪና የሚሉትን የሚሰማ እንዲሆን ይጠበቃል:: ነገር ግን፣ ከሌሎች ጋር ለመጫዎትና ለመስራት የሚያስችሏቸውን መንገዶችን በመፈለግና በመቀየስ በጣም ባተሌዎች ናቸው:: የህግና ደንቦችን መኖር ምክንያታዊነትና ጓደኛ ማለትስ ምን ማለት እንደሆነ መረዳትና መገንዘብ እየጀመሩ ናቸው:: ይህ ደግሞ፣ በተለይም የትምህርት ቤትን ህይዎት ገና ለሚጀምሩ ለጋ ሕጻናት ከባድ ስራ ነው::

## ልጅዎ ወደ ቅድመ-መዋዕለ-ሕጻናት ከመምጣቱ አስቀድሞ ሊያውቃቸው የሚገቡና ሊያደርጋቸው መቻል የሚገባውን አንዳንድ ነግሮች የሚያጠቃልሉ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ያልተገደቡ አንዳንድ ነገሮች:

- የሚፈልገውን ነገር መምረጥና የየዕለት ድርጊቶችን መከተል መጀመር፣ ለምሳሌ፣ ከመኝታ በፊት ተረት ማዳመጥን የመሳሰሉትን::
- የመጀመሪያ ስሙን ወይም ስሟን በጽሁፍ ላይ መለየት መጀመር::
- ከአዋቂ ሰው እንዴት እርዳታ መጠየቅ እንዳለበት ማወቅ::
- የሚወደውን መጽሀፍ በላይኛው ሽፋኑ አይቶ መለየትና ጮኽ ተብሎ እንዲነበብለት መጠየቅ::
- ስለፊደላት፣ ቃላት፣ ቁጥሮች፣ እና መቁጠር ለማወቅ መጓጓት መጀመር::
- ከሚታወቁ ዘፈኖች/መዝሙሮች ውስጥ የተወሰኑትን የቤት መምቻዎች ወይም ቃላት መደጋገም::
- መሰረታዊ ሁለት-ወይም ሦሥት-ደረጃ መመሪያዎችን መከተል፣ ለምሳሌ "ኮትህን አንሳ፣ ልበሰው፣ እናም ከበሩ ጋ ቁም::" የሚሉትን የመሳሰሉትን::
- ጮኽ ተብሎ ሲነበብለት ተረቶችን ማዳመጥ::
- መጽሃፍትን በጥንቃቄ መያዝ::
- በቤት ውስጥ አንዳንድ መሰረታዊ ህጎችን መከተል፣ ለምሳሌ፣ መጫዋቻ አሻንጉሊቶችን ከቦታቸው ማስቀመጥ፤፤

## ልጅዎ በቅድመ-መዋዕለ-ሕጻናት ውስጥ ምንድን ነው የሚማረው?

የትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራሙ፣ ለልጆች እድገት አስፈላጊ በሆኑት በሰባቱ የልጅነት አስተዳደጋዊ ትምህርት ልክና መጠን መሰረት ይዘጋጃሉ፡ ግለ-ሰብዓዊና ማህበረሰባዊ እድገት፣ ቋንቋና መጻፍ-ማንበብ፣ ስሌታዊ (ሂሳባዊ) አስተሳሰብ፣ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ፣ ሕብረትምህርት፣ ሥነ-ጥበብ፣ እና አካላዊ እድገትና ጤና ናቸው:: ተረትና መጽሃፍትን መውደድ፣ ሕጻናት ማንበብ ከሚጀምሩባቸው ዓመታት በፊት ሊያዳብሩት የሚገባው እንዱ በጣም አስፈላጊው ልምድና ዝንባሌ ነው:: ለዚህም ሲባል ነው፣ ቋንቋና ማንበብ-መጻፍ በልጅዎ የቅድመ-መዋዕለ-ሕጻናት ፕሮግራም ውስጥ ከፍተኛው ትኩረት ተስጥቷቸው የሚያዩት::

> ለጋ ሕጻናት የሆነ ነገርን በመሞከራቸው መወደስን/መሞገስን፣ የራሳቸውን ዓለም እንዲዳስሱም መበረታታትን ይፈልጋሉ::



*የንባብና የንግግሯ ተደጋጋሚ የዘወትር ድርጊትን ይፍጠሩ።*

*በየቀኑ ለልጅዎ ለማበብና ከሱም ጋር ለመነጋገር የሚሆን ልዩ ጊዜ ይመድቡ።*

## የልጅዎን በቅድመ-መዋዕለ-ሕጻናት የመማር ሁኔታ ለማገዝ ማበረታታት ከሚያደርጓቸው ጥቂት ነገሮች የሚከተሉትን የሚጨምሩ ሲሆን በነዚህ ላይ ብቻ የተገደቡ ግን አይደሉም፤

### ግለ-ሰብዓዊና ማህበረሰባዊ እድገት

- እሷ ራሷ እንድታደርግ ይፍቀዱላት። ልጅዎ ጧት ጧት ልብሷን እራሷ እንድትለብስ ጊዜ ይስጧት፤ ማታ-ማታም ለሚቀጥለው የትምህርት ቀን የሚሆኗትን ልብሶች በመምረጥ እዲታግዝ ይጠይቋት።
- ሥነ-ሥርዓት ይፍጠሩ ፥ ወደመኝታ ለመሄድ፤ በመኪና ለመሄድ መዘጋጀትን፤ ወደ ትምህርት ቤት ወይም የሕጻናት መዋያ ለመሄድ፤ ደህና ዋሉ ማለትን፤ ወዘተ የመሳሰሉትን የዘወትር ልምድ የሚሆኑ ሥነ-ሥርዓታዊ ተግባራትን ያስለምዱ። ሥነ-ሥርዓቶች ሕጻናት በቁጥርጥር ስርና ደህንነታቸው ተጠብቆ ያሉ ሆነው እንዲሰማቸው ያደርጋሉ።

### ቋንቋና መጻፍ-ማንበብ

- ተረት እንዲያወራ ያድርጉት። በአንድ ላይ ሆናችሁ እያነበባችሁት ባለው መጽሀፍ ላይ የሚታየውን ሥዕላዊ መግለጫ እንዲያስረዳ ያድርጉት።
- ንባብና ንግግርን የማዘውተር ልምድ ይፍጠሩ። በየቀኑ ለልጅዎ ለማንበብና ከሱም ጋር ለመነጋገር የሚሆን ልዩ ጊዜ ይመድቡ፤ ለምሳሌ ልክ ከእራት በኋላ ወይም ደግሞ ለመተኛት ዝግጁ ስትሆን። በማንኛውም ጊዜ ሲያነቡ፤ በታሪኩ ውስጥ ስለሚታዩት ገጸ-ባህሪያት፤ ሃሳቦች፤ እና ድርጊቶች ያውሩላት።
- ሥሙን በምልክትነት ያስቀምጡ። ልጅዎ ሥሙን ለመለየት እንዲችል ለመርዳት፤ በመኝታ ቤቱ በር ላይ በሚያስቀምጡት ምልክት ላይ ይጻፉት።
- ከዚያም ስሟን እንድትጽፍ ያድርጓት። ልጅዎ በደብዳቤዎች ወይም ለጓደኛ ወይም ለዘመድ በሚልኳቸው ካርዶች ላይ ሥሟን እንድትጽፍ ያድርጉ።
- የቃል ጽሁፍን ይጠቀሙ። ልጅዎ ሃሳቡን እንዲነግረዎት ያበረታቱት፤ ከዚያም እርስዎ ይጻፉለት። ወይም ሃሳቦቹን በሥዕል መልክ በወረቀት ላይ እንዲያስቀምጣቸው ያድርጉት፤ እርስዎም ወደዘምድ ጋ እንደሚላኩ አድርገው ምልክት ያደርጉበታል። ልጅዎ የምስጋና ደብዳቤ ወይም ለዘመድ ወይም ለጓደኛ የሚላክ የግብዣ ጥሪ እየነገረዎት እንዲጽፉለት ይጠይቁት።

### ሥሌታዊ (ሂሳባዊ) አስተሳሰብ

- የግሮሰሪ ሱቅን ያስተውሉ። በሱቁ ውስጥ የምግብ ሸቀጦች እንዴት እንደተደረደሩ ያመልክቱ፤ ጥራጥሬ በዚህ በኩል፤ የታሸጉ ፍራፍሬዎች በዚህኛው ጎን፤ የወረቀት ወጤቶች እዚህ ጋ፤ ወዘተ።
- ዘርፎችንና ሀረጎችን እዬጠቀሙ ያመልክቱ። ትኩረቱን በሥጋጃ ምንጣፉ ዙሪያ ባሉ ዘርፎች ላይ እንዲያሳርፍ ያድርጉት፤ ወይም የልብስ ቁልፎች (አዝራሮች)ን፤ ከለሮችን፤ ወይም መጫዎቻ ነገሮችን በተለያዩ አቀማመጦች ያዘጋጁቸውና ልጅዎ በተመሳሳይ ሁኔታ አቀማመጦቹን ተከትሎ ድርደራውን ያስቀጥለው እንደሆነ ይመልከቱ።
- መቁጠር ያዘውትሩ። በመኖሪያችሁና በግሮሰሪው መካከል ባለው መንገድ መሀከል፤ ሥንት ቁም የሚል የትራፊክ ማስቆሚያ ምልክቶች፤ የትራፊክ መብራቶች፤ ወይም የነዳጅ ማደያዎች እንዳሉ፤ ከልጅዎ ጋር አብረው ይቁጠሩ። ከቤተ-መጻሕፍት ለመቁጠር የሚሆኑ መጽሐፍትን ይፈልጉ፤ ከዚያም እርስዎ እያነበቧቸው ሳለ፤ በሥዕሉ ላይ ያሉትን ነገሮች አብራችሁ ቁጠሩ።

### ሳይንሳዊ አስተሳሰብ

- ተፈጥሮን የሚያሳዩ መጽሐፍትን ይፈልጉ። ከቤተ-መጻሕፍቱ ሂደው፤ ስለቢራቢሮዎችና እንቁርቦች፤ ስለዳይኖሶሮች፤ ስለወፎች የሚያወራ - እርስዎና ልጅዎ ሁለታችሁም የምትወዷቸውን እንስሳት የያዘ መጽሐፍ ይዋሱ። እንስሳት እንዴት እንደሚያድጉ፤ የት እንደሚኖሩ፤ እንዴት እንደሚቀየሩ፤ ወዘተ አውሩ (ተነጋገሩ)።
- ጥያቄዎቿን በመመለስ ልጅዎን ይርዷት። ልጅዎ "ለምን" የሚል ጥያቄ ስትጠይቅ በጥንቃቄ ያድምጧት፤ ከዚያም መልሶቹን በማፈላለጉ ሂደት እሷን ሊያሳትፉ የሚችሉበትን መንገዶች ያቅዱ፤ ለምሳሌ ስለጉዳዩ የበሰለ እውቀት ያለውን ሰው በማነጋገር፤ ከመጽሀፍ ውስጥ በመፈለግ፤ ወይም መረጃዎችን ለመሰብሰብ አንድ ላይ ሆነው በማፈላለግ።

### ሕብረት ትምህርት

- ስለቤተሰባችሁ አውሩ (ተነጋገሩ)። በዕድሜዎቻችሁ፤ በወርድና ስፋታችሁ መጠን፤ በጸጉራችሁና በዓይናችሁ ቀለም፤ እና በተሰጠዕዎ ችሎታዎቻችሁ (ለምሳሌ፤ የመዝፈን (የመዘመር)፤ስዕል የመሳል፤ አትክልተኛነት፤ የቧንቧ ስራ መስራት፤ መኪና ወይም ሞተር ብስክሌት መጠገን፤ ወዘተ) መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት አንስታችሁ ተነጋገሩ።
- ሰዎች ስለሚሰሩት ስራ ተነጋገሩ። እርስዎና ልጅዎ ቀኑን አብረው ሲያሳልፉ፤ ሰዎች ሌሎችን ለመርዳት ስራ ሲሰሩ ስለሚያዩአቸው ሰዎች ሁሉ ይወያዩ።

### ሥነ-ጥበብ

- የሕጻንነትዎን መዝሙር ያካፍሏት። በትምህርት ቤት ወይም በካምፕ ይዘምሩት የነበረውን መዝሙር ለልጅዎ ይዘምሩላት።
- እንደሚያስቡለት ያሳዩት። ልጅዎ በሚሰራው ስራ እና በምታበጃቸው ጥበባዊ እቃዎች ላይ ደስ እንደሚሰኙ ያሳዩአት።

### አካላዊ እድገትና ጤና

- አካላዊ እንቅስቃሴና ድርጊትን ያበረታቱ። ልጅዎ በቤተዎ ግቢ ወይም በፓርክ አካባቢ፤ ከቤት ውጪ ለመቆየት የሚያስችለው/የሚያስችላት ቢያንስ በሳምንት በርከት ያሉ ጊዚያት ይስጡ።
- ማብሰል ያስተምሩት። አትክልቶችን በማጠብ፤ የኬክ ሊጥን በማቀላቀል፤ የኩሽና እቃዎችን በማጻረቅ፤ ልጅዎ በምግብ ማዘጋጀት እንዲያግዝ በማድረግ እነዚህን ትንንሽ ጣቶች ስራ ያስይዟቸው።



**Maryland State Department of Education - Early Learning Office**

ለበለጠ ኢንፎርሜሽን በስልክ ቁጥር፡ 410-767-0335 ደውለው ያነጋግሩ።

Amharic